## **በናሽቪል ከተማ የኢሳት 4ኛ ዓመት በዓልን አስደግፎ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ስብሰባ ላይ የቀረበ አጭር (ንድፍ/ግርድፍ) ነግግር**
## **9/13/2014**
## **ከዶ/ር ሰይድ ሐሰን- Murray State University**

**Venue**: The *Luxury* Palace. 1185 *Antioch Pike*. *Nashville* TN 37211. English Line: 615-513-9730.

ክቡራትና ክቡራን ወገኖች፤

በመጀመሪያ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

በዚህ ስብሰባ ላይ በሁለት ጉዳዮች ላይ እንዳተኩር ተጠይቄአለሁ፡

1. ድህነት እየተስፋፋ ባለባት ኢትዮጵያ እንዴት በሁለት አሀዝ የኮኖሚ እድገት ሊኖር ይችላል?
2. እንደ ኢሳት ያሉ ነፃ እና የኛ የምለው የሚድያ አስፈላጊነትን በሚመለከት ነው፡፡

**አለ የሚባለዉን የኤኮኖሚ እድገትና ድህነትን በሚመለከት 2 ነጥቦችን በመጀመያ እንዳስቀምጥ ይፈቀድልኝ፡**

ሀ) ብዙውን ሰው የሚያደናገረው የኤኮኖሚ **አመታዊ ጭማሮን** (Economic Growth) እና **የኤኮኖሚ እድገት መለኪያን** ውይም ***የሰው እድገት መለኪያን*** (Economic Development) ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ ነው።

**Economic Growth** is indicated by an increase in that country's **gross domestic product**, or **GDP**.

የኤኮኖሚ ዓመታዊ ጭማሮ በቅርቡ የተሰሩ መንገዶችን፤ ድልድዮችን፤ ግድቦችን ደጋግሞ በማፍረስና እንደገና በመስራት ሊገኝ ይችላል። ለሕይወት በጣም አስፈላጊ ያልሆኑ ነገር ግን የውጭ ምንዛሬን የሚያስገኙ/የሚያሳድጉ ጥራጥሬዎችን አብልጦ በማምረት ይገኛል።

የደህንነት ጥበቃን፤ የሥለላ መረቦችን በመዘርጋት፤ ሰራዊቱን በመገንባትና የውታደራዊ በጀቱንና ክፍያዉን በማብዛት ሊገኝ ይችላል።

በእንድህ መልክ የሚገኝ የኤኮኖሚ ጭማሮ በአብዛኛው ጉዳት እንጂ የሕበተሰብ እድገትን፤ የሰው መለኪያ መመዘኛን ከፍ አያደርግም።

እደገት/***የሰው እድገት መለኪያ***- Economic Development- an increase in citizens' quality of life. 'Quality of life' is often measured using the **Human Development Index**, which is an economic model that considers intrinsic personal factors not considered in economic growth, such as literacy rates, life expectancy and poverty rates.

***የሰው እድገት መለኪያ***- **Human Development Index -** የኤኮኖሚ ጭማሮ መለኪያን ብቻ ሳይሆን፤ የትምህርት መስፋፋት መለኪያን፤ የድህነት መቀንስ መለኪያን፤ የፆታ ልዩነት መቅነስ መለካያን፤ የነፃነት መስፋፋት መለኪያን፤ እና ሌሎችን መለኪያዎችን ይጨምራል።

የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ በሚመለከት፤ በአገልግሎቱ የኤኮኖሚ ዘርፍ ትከሻ የተነሳ ጭማሮ ታይቷል። ሆኖም ግን ይህ አመታዊ ጭማሮ በሥለጣን ላይ ያለው መንግሥት እንደሚለው አይዶለም።

**በኢትዮጵያ የኤኮኖሚ ጭምሮ እንጂ የኤኮኖሚ እድገት የለም።** ለዚህ ማስረጃውም ኢትዮጵያ ከዓለም ሀግሮች 2ኛዋ የመጨረሻ ድሃ ሆና መመደቧ ነው።

ከዓመት -ዓመት ጨመረ የሚባለውና ችማሮውን የመቀለሉም ጉዳይ አሁን እያለቀበት ነው። እንዴት ብትሉኝ፤

1. መንግስት የሚቆልለው እድገት እየተጋለጠ መጥቷል፡፤ አበደሪ ደርጅቶችም ሆኑ የመንግስት ደጋፊዎች ሳይቅሩ የቁጥሩን መቆለል በጥያቄ እያነሱ ነው። የተከመረው ጭማሮ ዉሸት ነው እያሉ መጠየቅ ጀምረዋል፤
2. ከሚገባው በላይ የተለጠጠው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ (ፊኛ/ባሉን) በውጭ ምንዛሬ እጥረት፤ በኤክስፖርት ገቢ መዳከም፤ በመንግስት ፕሮጀክቶች መስተጓጎል፤ በኤሌክትሪክንክና ዉሃ መቋረጥ፤ በየግል ኢንቨስትመንት መቀጨጭ፣ እና በመሳሰሉት ችግሮች ክፉኛ እየፈነዳ ይገኛል።
3. በመግሥት የበላይነት የሚገፋው እድገት ውጤቱ ግሽበትን ማስከተሉ ስለበዛ፤ ገንዘብም እያጠረ ስለመጣ ማነቆው ላይ ደርሷል (ከሚጓዝበት ልኩ ላይ ደረሷል- it has reached its limits, hit a snag)፤
4. መንግስት በግሉ ኤኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው በደል ከሙብዛቱም በላይ፤ የልማታዊ መንግሥት የመለስ የዳቆናት ስብስብ የተበላሸውን ማርሹን መቀየር ስለማይችል፤ የተሰበረውን ፖሊሲ ሊያርቅ የሚችለው አቶ መለስ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየ፤ በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን እቅዱን ለማጠፍ አለመቻሉ Capacity for adjustment (flexibility)፤

**ለ) ዓመታዊ የኤኮኖሚ ጭማሪ ቆጠራን በሚመለከት**፤ በተወሰነ ድረጃም ቢሆን የአንዲት ሀገር ኤኮኖሚ እየጨመረ እያለ ድህነትና የሀብት ልዩነት እየተስፋፉ ሊሄዱ ይችላሉ! የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሲናጥጡ አብዛኘው ሕብረተሰብ በድህኘት እየተንፏቀቀ ሊሄድ ይችላል። ይህ በጽንሰ-ሃሳብም በተግባርም (በክስተትም) ታይቷል።

<u>==================</u>

<u>**የሁለት አሀዝ የኤኮኖሚ ጭማሪን በሚመለከት እኔም ሆንኩ ሌሎች የኤኮኖሚ ተመራማሪዎች በተለያዩ ጊዜና በተለያዩ ጽሁፎቻቸን በሰፊው ያሳየነው ስለሆነ፤በየረጅምና በዘላቂነት መልክ የኤኮኖሚ እድገት ምንጮችን ጠቅለል አድርጌ ላቀርብ፤**</u> የቀረውን በጥያቄና መልስ ጊዚያችን ለማብራራት እሞክራለሁ፤

የረዥም ጊዜ የኢኮኖሚ እድገትን በሚመለከት በታወቁ የኤኮኖሚ ጠበብቶች በተደጋጋሚ ተጠንተው የቀረቡ የኤኮኖሚ እድገት መንጮች/መመንዘኛዎች (መሰናክሎች/እንቅፋቶች) የሚከተሉት ናቸው።

**ለኤኮኖሚ እድገት ወሳኝ ነገሮች** - Sources and Determinants of Development/obstacles)- **ለዋቢነት የሚከተሉትን ይመልከቱ፤** Petrakos, et al,, Peterson Institute; Dewan and Hussien; Loayza & Soto; OECD; OECD2; summary/outline; )

1. **የተፈጥሮ ሀብት** ያላቸውና በአግባቡ ማበልጸግና መጠቀም የቻሉ ሀገሮች፤ Rich natural recourses- ግን የተፈጥሮ ሀብት ለብልጽግና ዋስትና አይደለም። ምሳሌ፤ 1) እምብዛም የተፈጥሮ ሀብት የሌላቸው ነገር ግን የበለፀጉ ሀገሮች፡ ጃፓን፤ ሆንግ ኮንግ፤ ታይዋን፤ ሌሎችም የእሳካንደኔቪያ ሀገሮች እንደምሳሌ ሊቆጠሩ ይችላሉ። 2) የተፈጥሮ ሃብት ያላቸው ነገር ግን ድሃ ሀገሮች፤ ሩሲያ፤ ኒጀሪያ፤ በርማ፤ አንጎላ.... እንደምሳሌ ሊቆጠሩ ይችላሉ። በአንድ በኩል የተፈጥሮ ሀብት መኖር እንደ እርግማንም (ሪሶርስ ከርስ)ሊቆጠር ይችላል!
2. **(መልካምና ጠቃሚ ወጣቶችን አሠልጥኖ የሚያቀርብ የትምህርት** ተቋማትን ማቋቋም/ማሰልጠን) **Good quality if human capital** attained with the provision of good education፤
3. (**ግኝት/**ፈጠራ - አዳዳስና የኑሮና ልማትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን ማድረግ የሚችሉና የቻሉ ሀገሮች) High technology, innovation, R&D፤
4. **የማይነቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ** (**ጥራት ያለው**) **ካፒታል/ንብረት፡** Physical capital and technological factors: the quantity and quality of physical capital
5. **(ጥሩ የጤና ጥብቃ ተቋማትን ማቋቋም**) Availability and access to good health care፤
6. **(በጎሳ መልክ አለመከፋፈላና** ብጥብጥን የሚያስከትሉ ግጭቶች አለመኖር) /Lack of ethnic fractionalization and lack of ethnic conflict፤
7. **(የባህር በር መኖር) Access to the sea**: Cross-country studies have shown that land-locked countries are poorer than those enjoying access to the sea፤
8. **መልካም አስተዳደርና ተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ** ያለባቸው ሀግሮች Stable political environmenት፤**– The Respect Of The Rule Of Law And Protecton On Cittizen's Rights፤ ቀለል ያለና ቀልጣፋ ቢሮክራሲ-** Low levels of public bureaucracy
9. **(የሙስና አለመብዛት፤** Low level of corruption and capacity for collective ፤
10. **(ለንግድ ዝግጁ መሆንና ለመዋዕለ ንዋይ ሥራ ዝግጁ ሆኖ መገኘት)** High Degree of Openness to trade and investment, including foreign direct investment፤
11. **Robust macroeconomic management** (የአጠቃልይ የኤኮኖሚ ፖሊሲው መረጋጋትና እራስን መቻል - በለይም ከመጠን በላይ የሆነ ግሽሽበት አለመኖር፤ የወለድ-አግድና የአራጣ ክፍያ

የተረጋጋና አበዳሪውን ዋስትና የሚሰጥ፣ ተበዳሪውን የማይበዘብዝ መሆን፣ በመምግሥት ደረጃ ለትውልድ በሚተፍ መልኩ እደኛ አለመሆን፣ የውጭ አገር እዳ በከፍተኛ ደረጃ አለመገኘት) Stable Macroeconomic policy Fiscal policy settings፣ እቅዶች የማሳኩ ከሆነ ለማጠፍ መቻል Capacity for adjustment (flexibility)

12. **(የግል ሐብትንና፣ የግለሰብ መብቶችን የሚስጠብቅ ሕግ መኖር፣ የፍርድ ቤቶችና የዳኝነት ሥራ ከፖሊቲካው ነጻ መሆን)**፣ Secured formal institutions, such as a well-functioning legal system, protection of property rights, tax and financial system and independent media፣
13. **ሐበርተሰባዊ ተሳትፎነትና የሕበርተሰባዊና የሀገር ወዳድነት/የመተባበር መንፈስ መኖር)** Capacity for collective action (political pluralism and participation, decentralization)'

**በቅርብ ጥናቶች የተጨመሩ፣**

14. **መልካም የገንዘብ መርሃ ግብር- Well-developed financial system** is likely to mobilise savings by channelling small savings of individuals into profitable large-scale investments, while offering savers a high degree of liquidity. It also provides insurance to individual savers against idiosyncratic risk through diversification, and it reduces the costs of acquiring and evaluating information on prospective projects, for example through specialized financial advisory services.
15. **በመገናኛ/ኢንፎርሜሽንና ቴሌኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ** ለመጠቀም ዝግጁ መሆን፣ **Information and communication technology** has contributed to economic growth both through rapid technological progress within the information and communication technology industry itself as well as, more recently, through the use of information and communication technology equipment in other industries. This has made an important contribution to growth in several of the faster growing countries.

**ላረጋግጥላችሁ፣ በሌሎች ሀገሮችና ኢትዮጵያም እንደምናየው፡**

1. የእርዳታ ሰጪ አገሮችኝና ድርጅቶችን ልብ ለምሳብ ተብሎ ያለ በቂ አስተማሪ፣ ያለ በቂ ቤተ-መጻህፍት፣ ያለ መማሪያ መሳሪያ እና መጻህፍት ዩኒቨርስቲዎችን አግተልትሎ በመክፈት የተገኘ እድገት የለም። ያለ ትምህርት ጥራት፣ ያለ ምርታማነት ያደገ ኤኮኖሚ የለም።
2. የግል ሚዲያውን በመጨፍለቅ፣ ጋዜጦችን በመዝጋት፣ ጋዜጠኞችን በማሰርና ከአገር በማሳደድ፣ ኢንተርነትንና የሶሻል ሚዳያን ዝርጋታን በመቆጣጠር፣ ሕዝብን ጨለማ ውስጥ በማስገባት በማንም አገር፣ በመቸውም ጊዜ የተገኘ እድገት ታይቶ አይታወቅም፣
3. የኤለክትሪክ ሃይልን፣ የዉሃ እና የተቴለፎን መገናኘዉን በመቆረጥ፣ የተስፋፋ እንዱስትሪ በየትም ሀገር አልነበረም። የኤሌክትሪክንና የቴሌፎን ዘርፉን በሞኖፖል ተቆታጥሮ ሕዝቡን እንዲበዘበዙ፣ ለሰላይነት እንዲዉሉ በማድረግ የተገኘ እደገት የለም።

4. ሀገርን በማፊያ አይነት ሙስና በመተብተብ የኤኮኖሚ ውድቀትን እንጂ እድገትን አምጥቶ አያውቅም።፡
6. ገንዘብን በማተምና በመርጨት ግሽበትን፤ የኑሮ ውድነትን ያስከትላል፤ እንጂ እድገትን አምጥቶ አያውቅም፤
7. የገንዘብ ምንዛሬን ደጋግሞ ከፍ በማድረግ (ድቫሉዌሽን በማድረግ) የዋጋ ንረትን በማምጣት የተገኘ እድገት የለም፤
8. ህዝበን እንደ እቃ በመሸጥ (ኤክፖርት በማደረግ)፤ የተማረውንና ጉልበት ያለውን (መሰደድ የሚችለዉን) የህበርተሰብ ክፍል አገሩን ጥሎ እንዲሰደድ በማድረግ ያደገ ኤኮኖሚ በየትኛዉም ጊዜና በየትኛዉም ዓለም ታይቶ አይታወቅም።
9. የግሉ ኤኮኖሚውን እንዲቀጭጭ ፖሊሲ አውጥቶ ተግባራዊ በማድረግ ዉድቀትን እንጂ እደገትን አምጥቶ አያውቅም።
10. የውጭ እርዳታን አግተልትሎ ማምጣ/ማስገባት ጥገኝነትን፤ በዙሪት ድህነት መጠመድን እንጂ፤ በዘላቂ መልክ፤ በአስተማማኝ መልክ የኤኮኖሚ እድገትን አምጥቶ አያውቅም።
11. የእንዱስትሪውን ዘርፍ በመደፍጠጥና ወደ ኋላ እንደጎተተ በማድረግ፤ የጥራ-ጥሬ እቃዎችን ለውጭ ንግድ በማቅረብ ባደረገ ፖሊሲ የተገኘ እድገት የለም።
12. ግልፅነትና ተጠያቂነት በሌለበት ሀገር ዘላቂ እድገት አይመጣም።
13. ነጋዴውን፤ ሠራተኛውንና ሕብረተሰቡን በክልል አጉሮ ንግድና የኤኮኖሚ ትሥር በግታት የተገኘ የኤኮኖሚ እደገት የለም፤ ጥፋት እንጅ፤
14. ወለድን ከዜሮ በታች ዝቅ በማድረግ ገንዘብ ቆጣቢውን የሚበዘብዝ ፖሊሲ ኤኮሚን አሳድጎ አያውቅም።
15. ሕዝብን ባለማሳተፍ የተገኘ እድገት የለም፤
16. የሀገርን ሕዝብ በስለላ መረብ ጠምጥሞ የያዘ ሥርዓት የኤኮኖሚ ድቀትን፤ ቆይቶም ቢሆን የሥልጣን መንኮታኮትን እንጂ እድገትን አምጥቶ አያውቅም!
17. የአካባቢ ብክለት በተስፋፋበት ሀገር የኤኮኖሚ እድገት ተግኝቶ አያውቅም።
18. የሀገርን የመሬት ሀብት ለውጭ ሀገር ቱጃሮች በርካሽ በመቸብቸብ የተገኘ እድገት የለም።
19. ድህነት በተስፋፋበት፤ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የህብረተሰብ ክፍል የውጭ እርዳታ ጥገኛ በሆነበት ሃገር፤ እድገት ሊኖር አይችልም።

የአንዲት አገር ኤኮኖሚ ማደጉ የሚገለፀው፤ *ሥራ ፈላጊዎች* ሥራ ሲያገኙና ሥራ አጥነት ሲቀንስ ነው። የአንዲት ሀገር ኤኮኖሚ ማደግ/መጨመርና የሥራ-አጡ መቀነስ የአንዲት ሳንትም ሁለት ገጾች ናቸው! ሁላችንም እንደምናውቀው ኢትዮጵያን ወጥሯት ያለው የሥራ አጥነት ችግር ነው። ስለዚህ፤ ስራ አጥነት በበዛበት ሀገር ኤኮኖሚው አድጓል ማለት የውሸታሞች የስነልቦና (ሞራል) ድቅት ውጤት ነው።

***ስለዚህ፤ መላው ሲጠፋው፤ ደሸሎመንታል ኤኮኖሚ፤ ልማታዊ መንግስት፤ የቻይና ሞደል፤ ጂኒ ቁልቋል ማደናገሪያ፤ የትም አያደርስም ።***

---

ለጨዋታ ያህል (ከአንድ ሁለት ዕማታት በፊት የሆነ- የተርፈ ጊዜ ካለ)፤ ከአንደኛው የአማርኛው የአሜሪካ ድምጽ ዘጋቢ ጋር የተደረገ የቃለ-መጠይቅ ግብ ግብ ፤

**ጋዜጠኛው፤** "የኤትዮጵያን የሁለት አኃዝ እድገት እንዴት ያዩታል?"

**መልስ (ከኔ):** እኔ በኢትዮጵያ ገጦ የሚታየኝ ድህነት እንጂ እድገት አይደለም!

***ጋዜጠኛው፤*** *ለዚህ ድምዳሜዎ መረጃ ሊሰጡኝ ይችላሉ?*

***መልስ* (ከኔ)**፤ *መረጃዎቹ ብዙ ናቸው፤* ከነዚም መካከል የተሰንራፋው ድህነት ነው፤ *ሥራ-*አጥነት ነው፤ የሕዝብ አገርን ጥሎ መሰደድ ነው፤ (ከዚህ በታች ከዘረዘኳቸው መካከል ጥቂቶቹንም ጠቀስኩላት) ከፈልግክ ደግሞ እኔም ሆንኩ ሌሎች የተቆለለውን የኤኮሞሚ እድገት እንደሌለ የሚያመላክቱ ብዙ ጥናቶችን አቅርበናል.....

***ጋዜጠኛው፤****(ጋዜጠኛው መልሶቼን አጥጋቢ ሆነው አላገኛቸውም።) ታዲያ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በስንት ያደገ ይመስለወታል?*

***መልስ* (ከኔ)**፤ *እድገቱ ይሄን ያህል ነው ብየ ልነግርህ አልችልም፤ ምክንያቱም ሁሉን ያካተተ መረጃ* ስለሌልኝ። *መንግሥትም የኤኮኖሚ እድገት የተመነበትን ዘዴም ሆነ የቁጥሮቹን ምንጮች በድብቅ* ስለሚይዘው። *ነገር ግን ከላይ እንዳልኩ፤ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ* (1) በደርግ ጊዜ ከነበረው ሆኔታ ጋር ሲታይ አድጓል። (2) እ.ኤ.አ. ከ2004 ጀምሮ ዓመታዊ ጭማሮ አድርጓል። ለዚህ ጭማሮ ዋናውን ሚና የተጫወተው የአገልግሎቱ ክፍል ነው።

(*ጋዜጠኛው አሁን መልሶቼ አጥጋቢ ሆነው አላገኛቸው*)

**ምመልስ (ከኔ- ቆጣ ባለ ድምፅ)**፤ ስማ ወንድሜ፤ ለተቆለለ ውሼት ከኔ መድህኒት የምትፈልግ ከሆነ እኔ *መድሃኒት (መፍትሄ) የለኝም። አለቀ!*

===========================

**የቅርብ ምሳሌ**፤ *ሀገሪቱ በብዙ መቶ ሽህ ቶን የሚሆን ስንዴ ከውጭ እያስገባች ባልችበት ወቅት፤ በበርካታ ሚሊዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ዜጋ የውጭ ሀገር እርዳታ ጥገኛ በሆነበት ጊዜ፤ በአዲስ አበባ ከተማ እንኳ ሕዝብ በቂ ዳቦ እንኳን ማግኘት ባልቻለበት ሁኔታ፤ በርካታ የተራቡ ዜጎች መኖራቸው የአደባባይ ሚስጢር ሆኖ እያለ፤ ባለፈው የግንቦት* 20 *በዓል በተከበረበት ወቅት፤ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ* *“ኢትዮጵያ በምግብ ሰብል እህል ምርት ራሱዋን ችላለች”* ብለው ሲሳለቁ ምን ትላላችሁ?

*ማንም የኤኮኖሚ ጠበብት ለእንደዚህ ያለው፤ አይን ያወጣ ቅጥፈት መፍትሄ ሊኖረው አይችልም!*

++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++

## ኢሳትና የነፃ ሚዲያ ተቋም (institution)አስፈላጊነት

እስቲ ለውይይታችን መንደርደሪያ እንዲሆኑን የተወሰኑ ነጥቦችንና ጥያቆዎችን ላንሳ፤

**1. መረጃ የኢሳት አድማጮች/ጎብኚዎች/ታዳሚዎች ስንት ናቸው?**

**መልስ፤**

**ሀ)** በየወሩ(በአማካይ)፤ 5,313,459 (ወርሃዊ ከፍተኛው፤ 7,587,568)

ለ) በየቀኑ (በአማካይ)፤ 171,402 (ቀናዊ ከፍተኛው፡ 289,165)

ታዲይ ይህን ያህል የኢሳት ታዳሚ እያለ፤ እንደ ኤሳት ያለ የተቋም ጅማሮ አጠንክሮ ማስኬድ ያቅታል?

**መልስ፤** (ከዚህ በታች እንዳሳየሁት)፤ ሁለት ችግሮች፡ (1) የገዝብ ወጪው ካባድ ስለሆነና (2) እንደ ኢሳት የነፃ ሚዲያ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ስልሆነ፤ ሀብትነታቸውም የሕዝብ ስለሆነ የፐብሊክ ጉድስ ችግር ስላለባቸው ነው።

**2.** ባሁኑ ጊዜ ጋዜጠኞች እየታሰሩ፤ እየተከሰሱ፤ ሀገር ጥለው እንዲወጡ፤ መደረጋቸውን፤ ጋዜጦችና መጽሄቶች እንዳይታተሙ እየተከለከሉ መሆናቸውን ታውቅላችሁ? ከመቸውም የበለጠ የጨለማ ዘመን እየመጣ ነው!

**3.** ይህ እየሆነ ሳለ አቶ ሽመልስ ከማል የተሰደደ ጋዜጠኛ የለም፤ ብሎ ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ መንገሩንስ ሰምታችኋል?

**4.** የአማርኛው የአሜሪካ ድምጽ የምታዳምጡ ካላችሁ፤ የአሜሪካ ድምጽ ባልደረባው ሄኖክ ሰማግዜርና የፒተር ህይሊየን ቅሌት ተከታትላችኋል? አበበ ገላውን ውሽታም ለማድረግ፤ ከሁን በፊት በአቶ አበበ ገላው ላይ የመግደል ዛቻ ሲደረግበት፣ አቶ ሀኖክ ጉድዩን ጠምዝዞና አጣሞ በማቅረብ ሊያታለን ሞክሮ ነበር!
አሁን ደግሞ **የአዙሳ ፓሲፊክ ዩኒቨርሲቲ** ለአቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ሊሰጥ የነበረውን የክብር ዲግሪ ስጦታና የእንግድነት ስነ-ሥርዓቱን መሳቡን/መሰረዙን በሚመለከት አቶ ሄኖክ ሰማግዜርና ፒተር ሀንላየን ያቀረቡትን የውሸት ድራማ እንደኔ ተከታትላችኋል?

**5. 13 ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የመከላከያ ሰራዊት አዛዦች የ 1997** ምርጫን አስደግፎ በህዝብ ላይ ባደረሱት ግድያና የጅምላ እስራት በተከሰሱበት የክስ መዝገብ ለስዊድን አለማቀፍ ወንጀል መርማሪ ፖሊስ መሰጠቱን ሰምታችኋል? በኔ አስተያየት ይህ ትልቅ ጅማሮ ነው; ጋዜጠኞችና የሬድዮ ጣባያዎች ሊዝግቡ ይገባል። ቢያንስ “እንዲህ ይባላል” ተብሎ መተውም ይገበዋል። ከ200 የማያንሱ ኢትዮጳዊያን የተገደሉበት፤ ከ40000 እስከ 60000 ኢትዮጵያውያን በእስር የታሰሩበት ጉዳይ ስለሆነ። ይህን ማን ዘገበው፡ ቮ ኦ ኤ፡ የጀርመን ድምጽ?

6. መንግሥት 350 000 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ለ 2 ሳምንት ያህል ሰብስቦ የሚሰጠውን የፕሮፖጋንዳ ሥልጠና ሰምታችኋል። ይህ ትልቅ ጉዳይ ነው። የጀርመን ድምጽ በአንድ የቅርብ እሁድ ዘገባው ቢያስተላለፈውም ቮ ኦ ኤ፡ ግን ችላ ብሎታል። ኢሳት ደጋግሞ እየዘገበው ይገኛል!

=======================================

ከዚህ በታች ያለው አጭር ንግግሬ ኢሳትን እንደ ነፃ ሚዲያ ታሳቢ (assume) በማድረግ ነው። አብዛኛው የእስካሁኑ የኢሳት የሥራ ጠባይም ይህንኑ ያመለክታል። የተለያዩ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላቸውን፤ ካገር ውጭም፤ ካገር ውስጥም ያሉትን አስተናግዷል። የመንግሥት ባለሥልጣናትንም እየጋበዘ ለማነጋገር ሞክሯል።

ከመንግስት ቁጥጥር ነጻ የሆነ የመገናኛ ዘዴ፤ ነፃ ሚዲያ/ፕረስ- ለሀገርና ለሕዝብ ልማት በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይ ባሁኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመን ነፃ ሚድያ እያስገኘ ያለው ጥቅም ብዙ ነው። የኢንፎርሜሽ ቴክሎጅን በሰፊው ተፎካካሪ ሀገሮችን ጥለው እንዲገሰግሱ እየረዳቸው ይገኛል። የሰውን ኑሮ ባጠቃላይ ዓለምንም እየለወጠ ነው።

**ስለዚህ ነፃ ሚዲያ የጋራ የህብረተሰብ ሀብት (public good) ነው! ምክንያቱም፡** ነፃና ጠንካራ የመገናኛ ዘዴ፤ ነፃ ሚዲያ ተቋም፤ነጻ ፕረስ፤ የግል ቴሌቪዝንና ሬድዮ ጣቢያውች መኖር፤

1. ዲሞክራሲ እንዲስፋፋ (እንዲፋፋ) ይረዳል፤ እንዳውም፤ ዲሞክራሲ ያለ ነፃ ሚዳያ ሊኖር አይችልም። ሁለቱን ነጣጥሎ ማየትም አይቻልም!

2. ንግድ እንዲስፋፋ፤ የገባያ ፉክክር እንዲኖርና እንዲጠናከር ይረዳል። የገባያ ፉክክር ሲኖር ደግሞ ኢኮኖሚው ያድጋል፤ አገርም ትበለፅጋለች።

3. እውነት የበላይነት እንዲኖራት ይረዳል::

4. ቅርስንና ታሪክን ዘክሮና ዘግቦ ለውርስ የማስቀመጫ መሣሪያ ይሆናል።
5. ዜጎች ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለመፈለግ እንዲወያዩ፤ እንዲከራከሩ፤ ይፈቅዳል/ይረዳል። በዚህም የተነሳ ዜጎች ብልህና ጠቃሚ ውሳኔዎችን እንዲወስዱም ይረዳል። ዜጎች ለሕብረተሰባቸውና ለሀገራቸው እድገት ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል። Media Serves Local Communities
6. ዜጎች በሀገራቸው ላይ የተፈጥሮ አደጋ፤ ተላላፊ በሽታ (ወረርሽኝ) ሲመጣ ባስቸኳይ ለሕብረተሰቡ መረጃዎችን ለማቅረብ፤ ሕብረተሰብም እንዲያውቃቸው ለማድረግ ይረዳል። ዜጎች እንድተባበሩም፤ የዜግነት ግዴታቸውን በፍጥነትና በጋራ እንዲወጡም የመገናኛ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል። Media and Society by improving the quality of education, informing the public about health threats and safe practices to avoid them, serving local communities by bringing attention to their needs, and in times of disaster,

providing information and sources of assistance to people displaced from their homes

7. የተጠፉፉ ዜጎችን፤ቤተሰቦችን፤ መተባበር የሚፈልጉ ሙያተኞችን ያገናኛል። በአካል መገናኘት ያልቻሉትን ሁሉ በቀላሉ ያገናኛል።

8. መንግሥት ሥራውን በትክክል እንዲሠራ ይረዳዋል; መንግሥት ለሕዝብ ተገዢ እንዲሆን ይረዳዋል። ዜጎች የመንግሥትን መጥፎም ሆነ መላካም ተግባሮች እንዲያዩ፤ እንዲገነዘቡና እንዲቆጣጠሩትም ይፈቅድላቸዋል፤ በአንፃሩም፤ አምባገነኖች ሕብረተሰቡን በተራ ውሼትና ፕሮፓጋንዳ ሕዝቡን ሊያጠምቁና ሊበርዙ ሲፈልጉ መንገዱን ይዘጋባቸዋል። በዚህም የተነሳ ክፍተቶችንም ይሞላል። As watchdog over public officials' actions, media helps fight and reduce corruption and crimes;

9. **ለነፃነት የሚደረገውን ትግል አቀጣጣይ መሳሪያ ሆኖ ያገልግላል። በጭንቅ ጊዜ (በጭንቅ ዘመን) የሕዝቡን አንድነት ሊያስተባብርና ለጋራ ትግሉ የመገናኛ መድረክ ሆኖ ያገለግላል።**

10. ፖለቲካዊና ህበረተሰባዊ ለውጦች እንዲመጡ/እንዲገኙ ይረዳል፤ አምባገነኖችን ከሥልጣን የማስወገጃ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፤ የሕብረተሰቦችን፤ የዜጎችን ችሎታ ያዳብራል (ኢምፖወር ያደርጋል)። Media Create Political Change

11. ነፃ ሚዲያ ኢንፎርሜሽንን ስለሚያቀብል እውቀት እንዲስፋፋ ይረዳል። ባለፉት 20 ዓመታት እንደታየው፤ በርካታ ሀገሮች አዲሱን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ፈጠራ) ተጠቅመው ሕዛባቸው በሥልጣኔና ዕውቀት እንዲገሰግስ አድርጓል። ደቡብ ኮሪያን ልምሳሌ መጠቀስ ይበቃል። media play a critical role in development by providing people with access to information; covering issues of relevance to those marginalized and living in poverty; reflecting impoverished peoples' perspectives in media coverage; and providing platforms where development issues can be discussed.

12. የግል ቴሌቪዥንና ሬድዮ ጣቢያውች መኖር አማራጭን ይሰጣል። ድምፃቸው ለተዘጋቸው ሀሳባቸውን የመግለጫ መንገድ፤ እንደ እንባ ጠባቂ ሆኖም ያገለግላል።

13. የመረጃ ማዕከሎችን በመፍጠር ትልቅ ሚናን ይጫውታል። መረጃና የመረጃ ተቋም የጋራ ሀብት ነው። መረጃ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው። መረጃ ኃይል ነው። መረጃ እውቀት ነው። እውቀትም የጋራ ሀብት ነው!

**So, a government that suppresses the media, is either anti-development, antisocial, anti-eduction፣ Procorruption, does not deserve to be in power**

**ከላይ የጠቀስኳቸው የነፃ ፕረስ፤ የነፃ ሚዲያና የመረጃ ተቋም መገኛ የሚያስገኛቸው ከፊል ጥቅሞች ናቸው። እነዚህ ጥቅሞች አንድ የጋራ የሆነ ጠባይ አላቸው። ይኸውም፤ ጥቅማቸው ለግል ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው ለጋራና ለሕዝብ ነው። በእንግሊዝኛው የPublic Goods ጠባይ ካላቸው መጠቀሚያዎች ይጠቃልላል ማለቴ ነው። ይህ የጋራ ጠባያቸው፤ ከጥቅማቸው ጋር ተያይዞም ቢያንስ ሁለት ችግሮችን ያስከትላል።**

***<u>1ኛውና ዝቅተናው ችግር</u>:*** ጠንካራ ሚዲያን ለማቋቋምና ቀጣይ በሆነ መንገድ ለማስኬድ የሚያስወጣው የገንዘብና የጉልበት ወጪው በጣም ብዙ መሆኑ ነው።

**ለምሳሌ፤ እንደ ኢሳት ያለውን ተቋም ለማቋቋምና ለማስቀጠል ባጭሩ፤**

1. ሀሳብን በማፍለቅ፤መሰረቱን ለመጣል፤የአየር ሞገዱን ለመምረጥ፤ ለማስተካከልና ለመሳሰሉት፤ ለሚደረገው ውይይት የሚጠፋው ጊዜና ገንዘብ፤

2. ለመግሥት ታክስና የመሥሪያ ፈቃድን ለማስገኘትና ለማደስ የሚወጣው እንግልትና የገንዘብ ወጪ፤

3. የሳተላይት ጣቢያን ለመከራየት የሚወጣው ገንዘብ፤

4. ቦታዎችን ለመከራየት፤ ክፍያውንም በጊዜው ለመክፈል የሚደረገው ወጪ፤

5. አስፈላጊ የሆኑትን የቴክኖሎጂ የማስተላለፊያ መሣሪያዎችን (broadcast equipment - master control switcher፤ satellite receivers, tape decks, and a transmitter፤ ካሜራዎችን፤ ኮምፒዩተሮችን፤ ሶፍትዌሮችን፤ ወ.ዘ.ተ.) ለመግዛት፤ አሮጌውችን ባዳዲሶቹ ለመቀየር በየጊዜው የሚወጣው ገንዘብ፤.

6. ሙያተኛ (ፕሮፌሽናል) ጋዜጠኞችን ለመቅጠር፤ ለማሰልጠን፤ የሰለጠኑትንም በአግባቡ ቀጥሮና ከፍሎ ለማሰራት፤ ሳይቋረጥ የሚደረገው ወጪ፤

7. መረጃን ለማግኘት የሚደረገው ክፍያ፤ ጋዜጠኞች ከቦታ ቦታ ሲጓዙ የሚደረገው ወጪና ክፍያ፤

8. የተሰበሰቡትን መረጃውች ሰብሰቦና ቀርፆ ለማስቀመጥ የሚደረገው ወጪ፤

   ለመርሀ-ግብር (programming) እና ለመሳሰሉት የሚደረገው ወጪ፤ ወ. ዘ. ተ.

**እንደነዚህና የመሳሰሉትን ለመሸፈን፤ ወጪው ከባድ ስለሆነ፤**

ሀ. አንዱ መንገድ፤ መንግስት ዜጎች ላይ ታክስ ጭኖ ወጪውን አጠቃሎ በመሸፈን ተቋሙን ማስቀጠል ነው። ይህ ክስተት በአፍሪካ፤ በኤሽያና በደቡብ አሜሪካ በስፋት ይታያል።

ለ. ሁለተኛው መንገድ፤ የሚዲያ ተቋሙ ከመንግሥት ካዝና ድጓሜ እንዲደረግለት በማድረግ፤ የቀረውን እራሱ ተቋሙ በንግድ (ቢዝነስ) የገቢ ምንጩን እንዲፈልግ ማድረግ ነው። ምናልባት እንደነ ቢ.ቢ.ሲ.ን ለምሳሌ ያህል መጥቀስ ይቻላል።

ሐ. ሦስተኛው፤ የግል ያልሆኑ፤ ለሕበረተሰብ አግልግሎት የተቋቋሙ የሬዲዮና የቴለቪዥን ጣቢያዎች (የሚዲያ ተቋማት)፤ ከመንግሥት ድጎማ እየተደረገላቸው፤ አንዳንድ የገዘብ ማስገኛ መንገዶችን እየፈላለጉ (ለምሳሌ ለኩባንያዎች ማስታወቂያን በማሰማትና በመለጠፍ) ወጪያቸውን ሽፋን ሲያደርጉ፤ በተጨማሪም በየጊዜው ኩባንያዎችንና ግለሰቦችን በመለመን፤ የማይናቅ ወጫቸውን ይሸፍናሉ። በአሜሪካ <u>NPR : National Public Radio</u> ን እና <u>**PBS:** Public Broadcasting **Service**</u>ን እንደምሳሌመጥቀስ ይቻላል።

*መረሳት የሌለበት ነገር፤ ኢሳትን ልዩ የሚድደርገው፤ሙሉ በሙሉ የእኛ-ለእኛ -ለሕዝባችን መሆኑ ነው። ኢሳት በግለሰቦች መዋጮ የሚደገፍ መሆኑም የበለጠ ክበድት ይሰጠዋል።*

*እንግዲህ እኛ፤ አልታደልንምና በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ኢሳትን ሊረዳ ቀርቶ፤ ለማዳፈን በበርካታ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር የሕዝብ ሀብት ያባክናል። ህወሀት/ኢሕአደግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጨለማ ውስጥ አጉሮ ለዘላለም ለመግዛት ያልቆፈረው ጉድጓድ የለም። በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሀብትን እያፈሰሰ የኢሣትን ሞገድ በጥለፍ ለማጥፋት/ለማዳፈን ያላደረገው ነገር የለም። ይህንን ሲያደርግም፤ ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት፣ የፕሬስ ነፃነት የሚፈቅደውን የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 29ኙን (ሐሳብንና አመለካከትን የመያዝና የመግለጽ ሙብት) እንደተለመደው በመጣስ ነው።*

*እንደዚህ ባልው ሁኔታ፤ ያለን አማራጭ የነጻ ሚዲያ ጥቅሙን በማሳየት እናንተ ኪሳችሁን እንድትዳብሱ "መለመን" የግድ ነው። እንደዚህ ያለው ልመና አስፈላጊም ነው፤ የተለመደም ነው። አገር ወዳዶችና ተለማኞችም ሳይሰለቹ በቋሚነት መልኩ መለገስ እንዳለባቸው ማስታወስም የግድ ይላል። አሁን ከፊታችሁ የቆኩትም ለዚሁ ነው።*

***<u>2ኛውና ትልቁ ችግር፤</u>*** *እንደ ኢሳት ያሉት የመገናኛ ዘዴዎች የሚያሰራጩት መረጃዎች እና ዜናዎች እንዲሁም <u>መዝናኛ</u> ዎች ... ግደታቸውን ለተወጡትም፤ ላልተወጡትም በጋራ ይደርሳሉ። የወር መዋጮቻቸውን ባለማድረገ ግደታቸውን ያልተወጡትም፤ ግዴታቸውን የተወጡም፤ የከፈሉም፤ ያልከፈሉም፤ ኢሳትን የሚወዱም፤ የማይወዱም፤ ኢሳትን ይሰማሉ፤ጥቅሙንም ይጋራሉ። ግደታችውን ያልተወጡትን መርጦ እንዳይሰሙ፤ ስርጭቱን እንዳይጋሩ፤ እንዳይጠቀሙ ማድረግ አይቻልም። በነፃ ተጠቃሚዎችን (በእንግሊዝናው፤**free** riders ተብለው የሚዘረፉትን ማለቱ ነው) ማግለል አይቻልም። ችግሩም በእንግሊዝኛው* "Free-Rider Problem" ይባላል። ይህ ችግር በእንግሊዝኛው ከ**"<u>nonexcludability</u>" criteria of a public good** ችግር ጋር ይጠቃልለላል።

በዚህም የተነሳ፤ እያንዳንዱ ሰው፤ በግለሰብ ደረጃ፤ አንድ ጊዜ ተቋሙ ከተመሰረተ በኋላ፤ "ለዚህ ሀብትነቱ የጋራ ለሆነ፤ ጥቅሙ የጋራ ለሆነ፤ ጉዳዩ የጋራ ለሆነ፤ የኔ ብቻ ላልሆነ.... ሌላው ይክፈለው እንጂ እኔ አልከፍልም፤ አላዋጣም" ሊል ይችላል! አልፎም፤ "ይህን የመሰለ "ግዳንግድ" ተቋም ከኔ ኪስ የምትፈልቀው መዋጮ ጋኑን ለመሙላት ለሚደረገው የውኃ ጋጋታ አንዲት ጠብታ ስለሆነች ማዋጣቴ ጉዳትንም፤ ጥቅምንም አያመጣም" የሚል ከንቱ አስተሳሰብን ያስከትላል። ይህ ጉዳይ በእንግሊዝኛው "**Drop-In-The-Bucket Problem**" ይባላል። ከዚያም አልፎ "ኢሳትን ከማዳመጥ የሚከለክለኝ፤ ማናባቱ ነው! እምቢ፤ አሻፈረኝ፤ አልከፍልም" የሚል መጥፎ አስታሰብንም ሊያስከትል ይችላል!

እንደምታውቁት እንደዚህ ያለው ችግርና አስተሳሰብ "የፋክክር በር (ወይም ባለቤት የሌለው በር) ሳይዘጋ ያድርና አደጋው **ለሁላችንም** ይደርሳል!" ከሚለው የአያቶቻችን ቁም-ነገራዊ አስተሳሰብ ጋር ይያያዛል። መልእክቴን ግልፅ ያደረግኩ ይመስለኛል፤ ኢሳትን እያንዳንዳችን በግል ተነሳሽነት ካልደገፍነው ኢሳት ሊኖር አይችልም! የኢትዮጵያ አይንና ጆሮ፤ የነጻነት ነፀብራቅ … እንዳይዳከም፤ እንዳይደፈን፤ መብራታችን ሆኖ እንዲቀጥል ከፈለግን፤ ቀጣይ በሆነ መንገድ መርዳት አለብን! ለሌላ የምንተወው ጉዳይ አይደለም!

በነገራችን ላይ ይህ ከላይ የነሳሁት ችግር በመገናኛ ዘዴ (ሚዲያ) ብቻ የተወነ አይደለም።

**ከላይ የጠቀስኩትን ለማጠናከር ያህል፤ እስቲ ኢሳት በዚች አጭር የለጋ እድሜው ከሸፈናቸው ትላልቅ ጉዳዮችና ከተጫወተው ታሪካዊ ሚናዎች አንዳንዶቹን ልጥቀስ፤**

1. በአረብ ሃገር የተከሰተውን ከፉ ስደትና በወገኖቻችን ላይ የደረሰውን በደል፤ በመዘገብ፤ በሥልጣን ላይ የለው ቡድን ያልደረሰላቸው መሆኑን በማጋለጥ፤ ኢትዮጵያዊያንን በማስተባበር የተቃውሞ ሰልፍ እንዲያደርጉ በማስተባበር የተጫወተው የማይናቅ ሚና፤
2. የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚያደርጉትን ትግል፤ በማስተጋባት ያደረገውና የሚያደርገው አስተዋፅዖ፤
3. የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚገርፈውን ሙስና ደጋግሞ በማጋለጥ እያበረከተ ያለው የማይናቅ ሚና፤
4. ህዝቦች በግፍ ቤቶቻቸው በቡልዶዘር ሲፈርስባቸው ሳይሰልስ ማጋለጡ፤
5. በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙትን የኢትዮጵያዊያን ሰቆቃን በመዘገ የተጫወተው ሚና፤
6. የሙስሊሞች የድምፃችን ይሰማ፤ የሙብታችን ይከበር ጥያቄን አስመልክቶ ያደረገው ሰፊ ሽፋንና የተጫወተው ሚና፤

7. ከጉራፈርዳ እና ከቤንሻንጉል-ጉምዝ የተፈናቀሉትን የብዙ ዜጎች የእሮሮ ድምጾች፤ የህወሃትን የዘር የማጥራት (Ethnic Cleansing) ወንጀል ሰፊ ሽፋን በመስጠትና በማጋለጥ የተጫወተው ሚና፤

8. የገዥው ፓርቲ አባላት የኢትይጵያን ሕዝብ ሲሰድቡ፤ ሲያዋርዱ፤ ሲዋሹ ድምፃቸውን በመቅረጽ ማጋለጡ። ለምሳሌ የአማራ ክልል ም/ ፕሬዚዳንት እና የብአዴን ጽ/ቤት ሃላፊ ተብየው አቶ አለምነው መኮንን የአማራውን ሕዝብ የሰደበበትን ማስታወስ ይቻላል።

9. በዋልድባ ገዳም መነኮሳት ላይ ህወሀት የደረሰውን በደል፤ እንግልትና መፈናቀል፤ የዘር ማጥራት ወንጀል፤ የመነኮሳቱን እሪታን በማስተጋባት በተካታታይ ያደረገው ሽፋን፤

10. በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በክረስትና ሀይማኖት ጉዳይ ውስጥ ያደርገውንና እያደረገ ያልውን ጣልቃ-ገብነት በማጋለጥ የተጫወተው ሚናና ሰፊ ሽፋን፤

11. ለሙብታቸው መከበር በሚታገሉ ዜጎቻችን፤ ጋዜጠኞቻችን፤ ወ.ዘ.ተ. እደረሰ ያለውን እስርና አፈና በማጋለጥ ያደረገው ሚና፤

12. የአቶ መለስ ሕልፈትን በሚመለከት ማንም ሳይቀድመው ያደረገው የዜና ዘገባና በህወሃት ላይ ያደረሰው ክስረትና ውርደት፤

13. መንግሥትን የከዱ ግለሰቦችን- ለምሳሌ፤ የኢት/ ቴሌኮሙኒኬሽን በሙስና መዘፈቅ፤ አድሎአዊና የጎሰኝነት የተሞላበት አስተደደርን በሚሚለከት፤ በብረታብረትን የቴክኖሎጂ ኮርፖሬሽን ተብየው ውስጥ፤ በኢትዮጵያ የጦርና መከላከያ መሥሪያ ቤት የሚደረገውን (እንደነ አቶ **ኤርምያስ ለገሰ (የመለስ "ትሩፋቶች" ባለቤት አልባ ከተማ)** ተስፋየ አጽብሀ ያሉና ሌሎችን ማስታወስ ይበቃል) እንግዶችን በእንግድነት በማቅረብ፤ በሰፊው እንደ፤ ደኩመንታሪ የሚሆን መረጃን በተከታታይ ማቅረቡ፤

14. ባጠቃላይ በሀገሪቱ ሰፍኖ ያለውን በደልና አድሎአዊ አስተዳደር ፤በተለይ የአንድ ጎሳ የባላይነት የሰፈነበት የሆነበትን ጉድ በተጨባጭና በመረጃ በተከታታይ ማቅረቡ፤በሚሊዮን የሚቆጠር አድምጭ እንዲሰማው ማድረጉ፤

15. የሶማሊው የክልል ፕሬዚደንት አቶ አብዲ ሞሃመድ አመር ከሶማሊ ጎሳ መሪዎች ጋር ያደረገውን ቅሌታዊ ውይይት፤ ከህወሃት ጋር ያደረገን መርዛዊ የፀረ አማራ ንግግርና የፀረ-ኢትዮጵያዊ የሶማሊ ዜጋ በደልን፤ በሶማሊ አስተዳደር የሰፈነውን ሙስና ወጣት አብዱላሂ ሁሴንን በእንግድነት በማቅረብ ያቀረበው ዘገባ/ቅሌት፤

16. ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የህበረተሰባዊ ተራድዖ መሬዎች፤ የሀሳባቸው መግለጫ መደረክ በመሆን የተጫወተውና እየተጫወተው ያለው ሚና፤

17. በሀገሪቱ ተንሰርፍቶ ያለውን ሙስና በማጋለጥና በመዘከር ያደረገውና የሚያደረገው አስተዋፅዖ፤

በኔ አስተያየት፤ ከላይ የጠቀስኳቸው የኢሳት ተግባሮች **በዋጋ የሚተሙኑ** አይደሉም! እርሰዎም ያውቁታል፤ ኢሳትን እያዳመጡም አድንቀዋል! ሌሎች የከፈሉም ሰምተውታል፤ አድንቀዋልም! ለመሆኑ ድርሻዎን

በትክክል ተውጥተዋል? ጥቅሙን ካወቁ፤ ከዚህ በላይ ያሰፈርኳቸው ችግሮችና ቁምነገሮች የገቡዎት ከሆነ ማለቴ ነው!

*__መደምደሚያ፤__*

እንግዲህ እኛ፤ አልታደልንምና በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ኢሳትን ሊረዳ ቀርቶ፤ ለማዳፈን በበርካታ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር የሕዝብ ሀብት ያባክናል። ህወሀት/ኢሕአደግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጨለማ ውስጥ አጉሮ ለዘላለም ለመግዛት ያልቆፈረው ጉድጓድ የለም። በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሀብትን እያፈሰሰ የኢሣትን ሞገድ በጥለፍ ለማጥፋት/ለማዳፈን ያላደረገው ነገር የለም። ይህንን ሲያደርግም፤ ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት፣ የፕሬስ ነፃነት የሚፈቅደውን የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 29ኙን (ሐሳብንና አመለካከትን የመያዝና የመግለጽ መብት) እንደተለመደው በመጣስ ነው።

እንደዚህ ባልው ሁኔታ፤ ያለን አማራጭ የነጻ ሚዲያ ጥቅሙን በማሳየት እናንተ ኪሳችሁን እንድትዳብሱ "መለመን" የግድ ነው። እንደዚህ ያለው ልመና አስፈላጊም ነው፤ የተለመደም ነው። አገር ወዳዶችና ተለማኞችም ሳይሰለቹ በቋሚነት መልኩ መለገስ እንዳለባቸው ማስታወስም የግድ ይላል። አሁን ከፊታችሁ የቆኩትም ለዚሁ ነው።

ወያኔ/ኢሕአደግ እንደ ኢሳት ያሉ ተቋማትን እንደጦር የሚፈራቸውም ያለምክንያት አይደለም፡፡ መላው ዓለም ለኢኮኖሚውና ለኅብረተሰባዊ ዕድገቱ እየተጠቀመበትና የኤኮኖሚ፤ የፖለቲካዊና የሕብረተሰባዊ እድገቱን በፈጠነ መልክ እያስኬደ ባለበት በዚህ የሥልጣኔ ግስጋሴ ዘመን፤ ወያኔ/ኢሕአደግ የሬዲዮ፤ የሳተላይት ቲቪ ስርጭቶችን፤ የኢንተርኔት፤ የእስካፕና ሌላውን ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴ መዝጋቱ፤ ለመዝጋት መጣሩ፤ መበሰሱ፤ ኅብረተሰቡ በጨለማ ውስጥ እንዲዳዝ ማደረጉ፤ የትምህርት ተቋሟት ጥራት መቀነሱ፤ በጣም የሚያስፍር ነው። በሥላጣን ላይ ያሉት ቡድኖችና ግለሰቦች የቱን ያህል፤ወደኋል የቀሩ መሆናችውን ያሳያል። እነዚህን የረከሱ ኋላ ቀሮች እንድንታገላቸው የሚያስችለን እንደ ኢሳት ያሉ ተቋማትን፤ የመረጃ ማዕከላትን በመመሥረትና በቋሚነት በመደገፍ ብቻ ነው።

በኔ አስተያየት ለመጀምሪያ ጊዜ የዲያስፖራው ሕብረተሰብ የሠራው ውጤታማ ሥራ ኢሳትን ማቋቋሙ ነው። ኢሳት በጨለማ ውስጥ እየማቀቀ ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ችላጭል ሰጥቶታል። ወደፊትም ይህ የመገናኛ ዘዴ የበለጠ እንድንተባበር፤ ለነጻነታችን የምናደርገው ትግላችን እንዲስምር፤ የሕዝባችን አንድነት እንዲጠነክር የሚረዳን፤ እንዳውም ህወሀት በቆፈረልንና እየቆፈረልን ባለው ጉድጓድ እንዳንገባ፤ እንዳንተላለቅ መገናኛና መወያያ፤ የመፍትሄ መፈለጊያ መደርካችን፤ መሳሪያችን ይሆናል ብዬ አጥብቄ አምናለሁ። የመልካም ዜጎች ትልቁ ሚና እና ትልቁ እርዳታ መሆን ያለበት እንደ ኢሳት ያሉ ተቋማትን መፍጠርና ማስቀጠል ነው።

ኢሳት እንዲቀጥል፤ እንዲያድግ፤ ቋሚ ሆኖ እንዲያገለግለን እያንዳንዳችን፤ ሁላችንም __- ማንም ሳይነግረን፤ ማንንም ሳንጠብቅ፤ ማንም ሳይለምነን፤ በባለቤትነት፤ በግል ተነሳሽነትና ሀላፊነት በተሞላው መንገድ፤ በቋሚነት ድርሻችንን መወጣት አለብን ብዬ አምናለሁ።__ እያንዳንዳችን ኢሳትን ለመጠበቅ ዘብ መቆምም አለብን።

You do not contribute for your own use since this is a public good. You do it for others, for your people back home, for your country.
You should feel special, you should be proud that you came here to cotribute and help the cause.

**ስላዳመጣችሁኝ አመሰጋናለሁ**